# ፋሺስዝም

*ለኢትዮጵያዊያን ፋሺዝምን ለመግለጽ መሞከር ለቀባሪው መርዶ ለመንገር መነሳት ማለት ነው። ለአብዛኛው ኢትዮጵያዊያን አያቶቻችን፣ ለጥቂቶቹ ደግሞ ወላጆቻችን፤ ለፋሽዝም ፓትርያርኩና ስሙን የሠጠው፣ ፋሽዝም ሲነሳ ስሙ አብሮ የሚነሳው፤ ቤኒቶ ሙሶሎኒ፤ ያለ የሌለ ጉልበቱን አሰባስቦ፣ ከፋሽዝም ባህሪዎች አንዱ የሆነውን፤የራሱን ዓላማ ለማስፋፋት ሌሎችን መውጋትና መውረር የሚለውን ሊያሳካ፤ ከጥይት እስከመርዝ ጭስ ያፈሰሰብን ስለሆነ ነው። በዚህ ጽሑፍ ለማድረግ የሞከርኩት፤ ፋሽዝም በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለውን መልክና ይዘት፤ ጠለቅ ባለ አሃዳዊ ምርምር፣ አጠቃላይ ግንዛቤ እንዲኖረን ነው። መልካም ንባብ።*


**በ**

**ጥቃት አልወድም**



*ረቡዕ ጥር ፳፬ ቀን ፳፻፱ ዓመተ ምህረት (2/1/2017)*
*ለዳግማዊ መላ አማራ አባላት ለጥናት የቀረበ*

## መግቢያ

ፋሺዝም፤ ከሥራ ፊት ዱርዬዎች ጀምሮ፤ ሥራ አጦችን በማቀፍ፤ ከፊል የሠራተኛው መደብ አባላትን አክሎ፤ በአብላጫው ደግሞ ንዑስ ከበርቴውን የያዘና፤ ከከበርቴውም ጥቂቶችን ያዘለ እንቅስቃሴ ነው። ፋሺዝም በርዕዩተ ዓለም ደረጃ፤ የከበርቴዎች ርዕዩት፤ ከበርቴዎቹ ራሳቸው የኛ አይደለም እስኪሉ ድረስ ለጥጦ የወሰደ ነው። ሕዝባዊ አለመሆኑ፤ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ድራሻቸውን በማጥፋቱ ሲገለጥ፤ በአንድ ወይንም በአንድ በተቧደኑ ጥቂት ግለሰቦች የተያዘውን መንግሥታዊ ግዛት ፈላጭ ቆራጭ አድርጎ በማስቀመጡ ይታወቃል። ማጠየቂያው፤ "ለመንግሥታዊ ግዛቱ ሁሉም ነገር መንበርከኩ፣ በዚያ ሥር ያለውን ሕዝብ ያገለግላል!"[፩] ማለቱ ነው። "ሁሉም ነገር ለመንግሥታዊ ግዛቱ! መንግሥታዊ ግዛቱን ማንም የሚቃወም የለም!"[፪] ነበር የሙሶሎኒ ስብከት።

አብዛኛዎቻችን የፋሺዝም ቃል ከቤኒቶ ሙሶሎኒና ከሂትለር ጋር እናያይዘዋለን። ትክክል ነው። ነገር ግን እኒህ ብቻ አይደሉም የፋሺዝም ቀንደኛ ባላቤቶች። በወቅቱ በናዚው ሂትለርና በፋሽስቱ ሙሶሎኒ ዙርያ፤ አውሮፓ በፋሺስት ፓርቲዎችና በፋሽስቶች የተጥለቀለቀች ነበረች። ( የፋሽስት ፓርቲዎች የነበሩባቸው ሀገሮች፤ ሃንጋሪ፣ ስፔን፣ ፖርቹጋል፣ እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ፣ ሮማንያ ) አሁን ፋሺዝም፤ በአፍሪካና በደቡብ አሜሪካ አይሎ ይታያል። በሂደት አጉስቶ ፒኖቼ፣[፫] ፍራንሲስኮ ፍራንኮ፣[፬] ጂን ቦዴል ቦካሳ፣[፭] አሳድ አባትና ልጁ፣[፮] የኪም ቤተሰብ - አያት አባትና ልጁ፣[፯] ሱሃርቶ፣[፰] ፖል ፖት[፱] እና ጆሴፍ ስታሊን[፲] ከመሠረቷቸው መንግሥታዊ ግዛቶች ጋር አብረው የሚጠቀሱ ናቸው።

የሞሶሎኒ የፖለቲካ ሕይወት ሂደት፤ በግራው ድርጅት ያጣቀሰና በጥራዝ ነጠቅ የሕዝባዊ ተቆርቋሪነት ርዕዩት ያለፈ ሲሆን፤ ሂትለር በአንፃሩ፤ ከሥር መሠረቱ ይሄን ክፍል በጠላትነት የፈረጀ ነው። ሁሉም በፋሽትነት የተስተዋሉ መሪዎች የሚወክሉት መደብ የላቸውም።[፲፩] የሠራተኛውንም ሆነ የከበርቴውን መደብ አይወክሉም። ከሁለቱም የተጣሉ ናቸው። "ሁሉን ነገር ለመንግሥታዊ ግዛቱ!" ሲሉ፤ የመንግሥታዊ ግዛቱን ሥልጣን በጃቸው ስለጨበጡና ያፈተታቸውን ማድረግ ስለሚቻላቸው፤ የማንም የበላይ ነን ባዮች ናቸው። ሕግ ማውጣቱም ሆነ መሻሩ የራሳቸው ጉዳይ ነው። ይህ እንዳለ ሆኖ፤ ንብረት መውረስ ንብረት መበተን፣ ጦርነት መክፈት ጦርነት ማቆም፣ ሰላማዊውን ሰው ማሰር እስረኛን መፍታት፣ ማሳደድ መግደል፣ ከጠባዮቻቸው የታወቁት ናቸው።

በሞሶሎኒና በሂትለር፣ በፒኖቼና በፍራንኮ እንደተገነዘብነው፤ ሁሉም ፋሽስቶች በሁሉም መስክ አንድ አይደሉም። አይሆኑምም። መሠረታዊ አሰራራቸውና ሁሉገብ ባህሪያቸው ነው መታየት ያለበት። ሁሉም ተንታኞች የፋሺዝምን ባህሪ ሲገልጹ፤ ከብሔርተኝነት ጋር ያያይዙታል።[፲፪] ይህ ብሔርተኝነቱ ግን፤ በኔ እምነት ለትንተና ሙቀት እንደተሠጣ ነው። በኔ እምነት፤ የራስን ወገን እየፈጁ ብሔርተኛ አይኮንም። በኔ እምነት ተቃዋሚዬ ነው ብለው፤ ትናንት አብሮ የነበረን የትግል ጓደኛ በገፍ እያሳደዱና እያረዱ ብሔርተኛ አይኮንም። በኔ እምነት የራስን ወገን መንደርና ሰው፤ እኔን ካልደገፋችሁ በማለት ጠራርጎ እያመከነ ብሔርተኛ አይኮንም። በግርጥ ብሔርተኝነትን ለራስ ድጋፍ ማሰባሰቢያ ተጠቅመውበታል። ራስንና የራስን ድርጅት ማስቀደም፤ ሀገርንና ወገንን ከማስቀደም ጋር አይዛመድም። የራስን ፓርቲ ጥቅም ለማስቀደም፤ ብሔርተኝነትን መጠቀም፤ ብሔርተኝነት አይደለም። ለምሳሌ በአውሮፓ በሞሶሎኒና ሂትለር ጊዜ፤ ብዙ የፋሺዝም ተከታይ ሀገሮች ነበሩ። እኒህን ፋሺስቶች በምንም መለኪያ ብሔርተኞች ማለት አይቻልም። አንገታቸውን ለሞሶሎኒ ወይንም ለሂትለር ደፍተው፤ ሀገራቸውን ለሞሶሎኒና ሂትለር የግባቸው ማራመጃ ያደረጉ ነበሩ። ለራሳቸው ሹመት ሲሉ፤ የገዛ ሀገራቸውን ለኒህ ታላላቅ ፋሽስቶች አገልጋይ አደርገዋል። ታዲያ እኒህ ፋሽስቶች ብሔረተኛ ሊባሉ ነው? ለዚህ ነው ብሔርተኝነትን በሚመለከት ፍርዱ አልጠራም የምለው።

## ፋሺዝም

እስኪ መሠረታዊ የሆኑትን ባህሪያት እንመልከት። ፋሺዝም ፍርሃትን ያነገሠ፤ አምባገነን አስተዳደር ነው።[፲፫] በፋሽስታዊ አስተዳደር፤ የሰው ሰውነቱ ሳይሆን፤ የተደፋ ጭንቅላቱና የጎበጠ ጀርባው ናቸው መታየት ያለባቸው።

ፋሺዝም፤ አንድ ብቸኛ ገዥ ሆኖ፤ ተወዳዳሪ ወይንም ተቃዋሚ የሚባል፤ መኖር አይደለም ትንፋሹ እንኳን እንዳይደመጥ፤ ያለ የሌለ ድንጋይ ሳይቀር ተፈንቅሎ፤ ሁሉም ነገር የሚኮንበት አምባገነናዊ ግዛት ነው።[፲፬]

ፋሺዝም አዋጅ የሚደረደርበት፣[፲፬] ለሀገሪቱ ሳይሆን ለገዥዎቹ የሚመቹ ሕጎች፤ በይስሙላ ፓርላማ የሚወጡና የሚሻሩበት ግዛት ነው።[፲፭] የውሸቱ ምርጫ እንኳን ይቻላል ተብሎ በማይታሰብበት ሁኔታ የሚካሄድበት ግዛት ነው። በራሱ መለኪያ ሕግና ደንብ እንኳን ሳይገደድ፤ ከዚያ ውጪ የሚገዛ ፍጹም አረመኔ፣ ፍጹም አምባገነን የሆነ መንግሥት የነገሠበት ነው።[፲፮]

በተደጋጋሚ ሥልጣን የወሰዱት በምርጫ ሳይሆን፤ በማጭበርበር ነው።[፲፯] መፈንቅለ መንግሥት ይሆናል፣ አዋጅን ተከትሎ ሥልጣን በመዝረፍ ይሆናል፣ ያለውን መንግሥት ሕጋዊ አይደለም ብለው በማታለልም ይሆናል፤ በጠቅላላው ሥልጣናቸውን ያገኙትና የሚገፉበት፤ ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ነው። ከዚያ አከታትለው የግለሰብ ተክለ ሰውነት እንዲገን ያደርጋሉ።[፲፰] ሙስናና አድልዎ መታወቂያቸው ነው።

ከዚህ ተነስተን፣ ለምንድን ነው ፋሺዝምን አጣርተን ማወቅ ያለብን? ከኛ ጋር ምን ግንኙነት አለው? በኛ ሀገርስ ፋሺዝምን ያካሄደ ወይንም እያካሄደ ያለ መንግሥት አለ ወይ? የሚሉትን በመመርመር፤ ለግንዛቤያችን ቅርብ አድርገን እንመለከታለን።

የፋሺዝምን ትርጉም አጣርቶ ማወቅ፤ የፋሽስትን ገፅ ትክክለኛ ገጽታና ባህሪ ከመረዳት በተጨማሪ፤ እንዴት ይሄን ፋሽስት ገፅ መታገል እንደሚገባ በትክክል ይመራል። ለምን ቢሉ፤ የፋሺዝምን ትርጉም እያንዳንዱ ግለሰብ በየቦታው እንዳሻው ትርጉም ሠጥቶ ሲወረውረው፤ የትግሉን ውስጠ ባህሪ አለመረዳትን እና፤ ብሎም የትግሉን ትክክለኛ አቅጣጫ አለመያዝን ስለሚያስከትል ነው። ግልጽ ባልሆነ ጠላት ላይ የሚወረውሩት ደንጋይ፤ የት እንደሚወድቅ አይታወቅም፤ ተመልሶ ራስን ሊፈነክት ይችላል። በተለይም ታጋዮች በትክክል ያለውን ሀቅ ለመረዳትና ለቀጣዩ ትውልድም፤ በኛ ጊዜ የነበረውን ሀቅና የትግላችንን ሂደት አብራርቶ ለማስተማር፤ የፋሺዝምን ትክክለኛ የምንነት ግንዛቤ መያዙ፤ ትኩረት ሊሠጠው ይገባል።

በመጀመሪያ አሁን በኢትዮጵያ ያለው ገዥ ክፍል፤ የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር አይደለም። ትግሬዎችን ከማን ነው ነፃ የሚያወጣቸው? ከራሱ ከገዥው የትግራይ ቡድን? አይሆንም። እናም የትግሬዎች ነፃ አውጪ ቡድን ማለት ትክክል አይደለም። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ይሄን ግንዛቤ አጥብቀን እንረዳ። ቀጥሎ ደግሞ፤ ትግሬዎች ሆነው በትግሬዎች ስም እየገዙ ስለሆነ፤ ወደድንም ጠላንም፤ የትግሬዎች ገዢ ቡድን ነው። እናም የትግሬዎች ገዢ ቡድን ብለን መጥራቱ ትክክለኛና ተገቢ ነው። ሽፋፍነው ቢናገሩት የሚያወናብደው ተናጋሪውንና አድማጩን እንጂ፤ የተነገረለትን ወይም የተነገረበትን አይደለም።

አሁን አንዳንዶች የትግሬዎችን የቡድን መንግሥታዊ ግዛት ፋሽስት፤ እንዲያውም የለየለት! ሲሉ ይደመጣሉ። አንዳንዶች ደግሞ ለምን ፋሽስት ትላላችሁ? "ጨካኝ የሆነ ሁሉ ፋሽስት አይባልም!" ይላሉ። መስፈርቶችን አያሟላም በማለትም ይከራከራሉ። መልካም። ታዲያ ግንዛቤውን አብረን እናብጠልጥለውና፤ አብረን ስም እናውጣለት። እውነት ይሄን መንግሥት ፋሺስት ማለት ይቻላል ወይ? ፋሺዝም ምንድን ነው? ፋሽዝም እንዴትና በምን ሁኔታ ይከሰታል? መሠረቱ ምንድን ነው? ባህሪዎቹ ምንድን ናቸው? መገለጫዎቹስ? የሚሉት ጥያቄዎች ራሳቸው የሚያደናግሯቸው ደግሞ አሉ። እስኪ ከሥር መሠረቱ ጀምርን የፋሽስት ወለፈንድን ትርጉምና ቦታ እንመልከት።

መቼም ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው ስለሚባል፤ ቡዳ እንዳንባል፤ በመጀመሪያ ባለቤቶቹ የሠጡትን ትርጉም እንመልከት።

***"Everything in the State, nothing outside the State, nothing against the State"***

***Mussolini***[፲፱]

*"ሁሉም ነገር ለመንግሥታዊ ግዛቱ፣ ከመንግሥታዊ ግዛቱ ውጪ ምንም የለም፣ መንግሥታዊ ግዛቱንም የሚቃወም ምንም ነገር አይኖርም።"*

*ሙሶሎኒ*

*"It is thus necessary that the individual should come to realize that his own ego is of no importance in comparison with the existence of his nation; that the position of the individual ego is conditioned solely by the interests of the nation as a whole ... that above all the unity of a nation's spirit and will are worth far more than the freedom of the spirit and will of an individual . . . This state of mind, which subordinates the interests of the ego to the conservation of the community, is really the first premise for every truly human culture . . . we understand only the*

*individual's capacity to make sacrifices for the community, for his fellow man."*
***Adolph Hitler**, 1933*[፳]

*“እናም ግለሰቡ፤ ከብሔሩ ( እዚህ ላይ መንግሥታዊ ግዛቱ ) ሕልውና ጋር ሲነጻጸር፤ የግለሰቡ “እኔነት” ከግምት ውስጥ እንደማይገባ እንዲገነዘበው አስፈላጊ ነው። የግለሰቡ “እኔነት” ቦታ ከመንግሥታዊ ግዛቱ ጥቅም አንጻር ብቻ የሚመዘን ነው . . . ከሁሉም በላይ፤ የመንግሥታዊ ግዛቱ የመንፈስና የፍላጎት አንድነት፤ ከአንድ ግለሰብ መንፈስና ፍላጎት በጣም የላቀ ዋጋ አላቸው . . . የዚህ ግንዛቤ አያያዝ፤ የግለሰቡን የእኔነት ጥቅም ለኅብረተሰቡ ሕልውና አሳልፎ መሥጠት፤ ለያንዳንዱ ትክክለኛ የሰው ልጆች ባህል የመጀመሪያው ቃል ኪዳን ነው . . . እኛ የምንረዳው፤ ግለሰቡ ለኅብረተሰቡ፤ አብረውት ላሉት ጓደኞቹ ሊያደርግ የሚችለውን መስዋዕትነት ብቻ ነው።”*

*አዶልፍ ሂትለር፣ በ ፲ ፱ ፻ ፳ ፭/፮ ዓመተ ምህረት*

ቀጥለን ደግሞ በዚያ ወቅት ከነበረው የጣሊያን ስንክሳር የሠጠውን ትርጉም እንመልከት፤

"The State not only is authority which governs and molds individual wills with laws and values of spiritual life, but it is also power which makes its will prevail abroad.... For the Fascist, everything is within the State and... neither individuals or groups are outside the State.... For Fascism, the State is an absolute, before which individuals or groups are only relative."

Fascism is an authoritarian form of government opposed to extending civil liberties (and even curtailing or removing existing ones) in exchange for radical empowerment of business and economy. Fascist countries usually have elite armies, and see war as a sport or honour event. Lax views on imperialism, a holier-than-thou immigration discrimination policies (first generation immigrants to work for half minimum wage), and everything 'for the state'.

**fascism**
From Encyclopedia Italia 1932: [፳፩]

““መንግሥታዊ ግዛቱ፤ በሕግና በመንፈሳዊ ሕይወት፤ የግለሰብ ፍላጎትን ገዥና ቀራጭ ብቻ ሳይሆን፤ በውጪ ሀገር ላሉትም የራሱን ፍላጎት የበላይነት የሚያረጋግጥ ኃይልም ጭምር ነው . . . ለፋሽስቱ፤ ሁሉም ነገር በመንግሥታዊ ግዛቱ ውስጥ ነው። እናም . . . ግለሰቦችም ሆኑ ቡድኖች፤ ከመንግሥታዊ ግዛቱ ውጪ አይደሉም . . . ለፋሺዝም፤ መንግሥታዊ ግዛቱ፤ ግለሰቦችም ሆኑ ቡድኖች፤ ከሱ ፊት አንጻራዊ ብቻ የሆኑበት ፍጹማዊ ነው።”

ፋሺዝም፤ ለንግድ ተቋማትና ለምጣኔ ሀብት ስምሪት ያልተለመደ ፍጹም የበላይነት ሲል፤ የሕዝብን መብቶች የሚጠቀጥቅ ( የነበሩትንና ያሉትንም ሕጎች የሚያስወግድ ) ፈላጭ ቆራጭ የመንግሥት ዓይነት ነው። ፋሺስታዊ መንግሥታት ያሉባቸው ሀገሮች፤ በጣም የላቀ ሥልጡንና የተለዬ ወታደራዊ ክፍል አላቸው። እናም ጦርነትን እንደ ስፖርት ወይንም የጀግንነት ክስተት አርድገው ይመለከቱታል። በኢምፔሪያሊዝም ላይ የለዘበ አመለካከቶች ሲይዝ፤ ከማንም በላይ ነን፤ እና ሁሉም ነገር ‘ለመንግሥታዊ ግዛቱ’ የሚል፤ በስደተኛ ላይ ዘረኝነትን ያነገሠ ( የመጀመሪያ ተሰዳጆች ትውልድ በግማሽ ደሞዝ ይሥሩ የሚል ) መመሪያ አለው።

ፋሽዝም
ከጣሊያን ስንክሳር ፲፱፻፳፭/፮ ዓመተ ምህረት

ቀጥለን ደግሞ ማርክሲስቶች የሚሠጡትን ትርጉም እንመልከት፤

Fascism is right-wing, fiercely nationalist, subjectivist in philosophy, and totalitarian in practice. It is an extreme reactionary form of capitalist government. [፳፪]

https://www.marxists.org/glossary/terms/f/a.htm

ፋሽዝም የቀኝ ክንፍ፤ ያከረረ ብሔርተኛ፣ በፍልስፍና ረገድ በራሱ ፍላጎት እምነትና ተመክሮ የሚመራ፣ እና በተግባር ፍጹም አምባገነን ነው። ጽንፈኛ አክራሪ የሆነ የከበርቴዎች የመንግሥት ዓይነት ነው።

https://www.marxists.org/glossary/terms/f/a.htm

"A form of political practice distinctive to the 20th century that arouses popular enthusiasm by sophisticated propaganda techniques for an anti-liberal, anti-socialist, violently exclusionary, expansionist nationalist agenda."

Robert Paxton, a professor emeritus of social science at Columbia University in New York widely considered the father of fascism studies[፳፫]

“ለ፳ኛው ክፍለ ዘመን ልዩ የሆነ፤ ለፀረ-እኩልነትና ፀረ-የግል ነፃነት፣ ለፀረ-ሶሺያሊስት፣ ተጋፊ እና ብቻነትን፣ ሌሎችን ለማጥቃት የተዘራ ብሔርተኝነትን በተራቀቀ የፕሮፓጋንዳ ቅንብሮች፤ ሕዝባዊ የጋለ ስሜትን የሚያነሳሳ አንድ የፖለቲካ ክንውን ዓይነት፤”

ሮበርት ፓክስተን፤ በኒው ዮርክ ከተማ፣ ኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲ፤ የፋሺዝም ጥናት ባላባት ተብለው የሚታወቁ፤ ነባር የሶሺያል ሳይንስ ፕሮፌሰር

Fascism ‘is the pursuit of a transcendent and cleansing nation-statism through paramilitarism’. Michael Mann[፳፬]

ፋሽዝም፤ “ከሁሉም የላቀ፤ በወታደራዊ ቀመስ ጉልበት፤ ሌሎችን በማጥራት ለተለዩ ሰዎች የብሔር-መንግሥታዊ ግዛት ምስረታ ጥረት ነው።”

ሚካኤል ማን - ( ማርክሲስታዊ ተንታኝ )

አንድ ምሁር፤ ፋሽዝምን በአስራ አራት ነጥቦች ከውነው አስቀምጠውታል። እንዲህ ሲሉ፤

14 identifying characteristics of Fascism by Political scientist Dr. Lawrence Britt. ("Fascism Anyone?," Free Inquiry, Spring 2003, page 20) [፳፭]

፲፬ የፋሽዝም መታወቂያ ባህሪዎች፤ በፖለቲካ ሊቅ ዶክተር ሎረንስ ብሪት
( “ፋሽዝም! ባገር ሰው አለ? ነፃ ምርምር፣ ጸደይ ፲፱፻፺፭/፮፣ ገጽ ፳ )

1. Powerful and Continuing Nationalism: / ጠጣር ኃይለኛና የማያባራ ወገናዊነት

   ፋሺስት መንግሥታት ወገናዊ መፈክሮችን፣ ከኔ በላይ የለም ባይነትን፣ ወገናዊ ጉራና ፉከራዎችን፤ እኛ ወርቆች ነን ባይነትን፤ የየዕለቱ ሕዝብን ማደንቆሪያ ያደርጋሉ። የራሳቸውን ሰንደቅ ዓላማ በየምናምኑም ሁሉ ይከታሉ። ባደባባይ ልታይ ልታይ ባይነት ያጎላሉ። *(ደንቁረን ጆሯችን ተዘግቷል - የኔ)*

2. Disdain for the Recognition of Human Rights: ለሰብዓዊ መብቶች ዕውቅና ንቀትና ጥላቻ

   “ጠላት” ለሚለው ባለው ፍርሃትና ለደህንነቱ አስፈላጊ ነው ብሎ ስለሚያምን፤ በፋሽስት መንግሥታዊ ግዛት ሥር ያለ ሕዝብ፤ ሰብዓዊ መብቶች፤ “ጠቃሚ” ስለሆነ ባንዳንድ ሁኔታዎች ሊተው ይችላል፤ በሚል እንዲስማማ ተደርጓል። ሕዝቡ ያለፍርድ ግድያዎችን፣ ለረጃጅም ያልተወሰነ ጊዜያት መታሰሮችን፣ አድፍጦ ነፍስ ማጥፋቶችን፣ በስርቤት ማጎሳቆልን እንዳላዩ ሆነው ማለፍና፤ እንዲያውም “ይሁን!” ብሎ መቀበሉን ይገፉበታል። *(ኧረ! ይሄስ የኛው የምናውቀው ነገር ነው - የኔ)*

3. Identification of Enemies/Scapegoats as a Unifying Cause: የጠላቶች/የማሳበቢያ መታወቅ አንድ ላይ አሰባሳቢ ምክንያት ሆኖ መወሰድ

   ሕዝቡ “የጋራ ጠላት” ተብሎ የተለደፈበትን አሳቦ፤ በዘር፣ በመንደርተኝነት፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከታቸው ነፃነትና እኩልነት ፈላጊ በሆኑ፣ በሕዝብ አፍቃሪዎች፣ *(በነፍጠኞች፣ በደርጊስቶች፣ በአማራዎች - የኔ)* በመሳሰሉት ላይ በወገንተኝነት አብሯቸው እንዲቆም፤ ያስዘፍኑታል።

4. Supremacy of the Military: ፍጹማዊ የጦር ሠራዊቱ የበላይነት

ሀገር አቀፍ ችግሮች ወጥሮ ቢይዛቸውም፤ ወታደራዊ ክፍሉ ሚዛኑን ያዛባ መንግሥታዊ ውጪ፣ ድጎማም እየተሠጠው፣ ያገሪቱ ችግር ወደ ጓዳ ይወረወራል። ወታደሮችና ወታደራዊ አገልግሎት እንደ ጣዖት ይመለካሉ። (ኢጋዚ - የኔ)

5. Rampant Sexism: ይሄ ነው ተብሎ ወሰን የሌለው የወንድ የበላይነት መንገሥ

የፋሽስት ሀገር መንግሥታዊ መዋቅሩ ከሞላ ጎደል በወንዶች ብቻ የተጥለቀለቀ ነው። በፋሽስት መንግሥት ሥር፤ የቆየው ባህላዊ የፆታዎች ሚና የበለጠ እንዲጠጥር ይደረጋሉ። ፅንስን ለማስወረድ ያለው ተቃውሞ ከፍተኛ ነው። ፀረ-የተመሳሳይ ፆታ ተፋቃሪዎች ሕጎችና በርጋጊነት ከሀገራዊ ጸጥታ ጋር፤ ቦታው ከፍ ያለ ነው። (ለዚህ ነጋሪ አያሰፈልገንም - የኔ)

6. Controlled Mass Media: የሕዝባዊ ዜና መለዋወጫ ፈሰሶችን ማፈን

አንዳንድ ጊዜ የሕዝባዊ ዜና መለዋወጫ ተፋሰሶች በመንግሥት ይዘጋሉ። በሌላ ጊዜ ግን በመንግሥታዊ መመሪያ ይታፈናል። ወይንም የዚህ ተፋሰስ ደጋፊዎች በሆኑ ሥራ አስኪያጆች ይዘጋሉ። ይህ የአፈና ጉዳይ፤ በተለይ በጦርነት ወቅት በጣም የተለመደ ነው። (ጋዜጠኞች ተሰደው ባለቁበት ሀገር!!! እስር ቤቶች ይመስክሩ!!! - የኔ)

7. Obsession with National Security: በሀገር ጸጥታ ላይ እንቅልፍ ማጣት

ፍርሃት፤ መንግሥቱ በሕዝቡ ላይ የሚጠቀምበት የማነቃቂያ መሳሪያው ነው። (ጌታቸው ረዳን ማን ሾመው - የኔ)

8. Religion and Government are Intertwined: ሃይማኖትና መንግሥት ተጣምረዋል

በፋሽስት ሀገር ያሉ መንግሥታት፤ በሀገሪቱ ያለውን የብዙኀን ሃይማኖት የሕዝቡን አመለካከት ለመንዳት ይጠቀሙበታል (በኛ ሀገር ሁሉንም)። ሃይማኖታዊ ቃላትን መጠቀምና ማስመሰሉን፤ ምንም እንኳን የሚሠሩትና የሚናገሩት ሰማይና ምድር ቢሆንም፤ መሪዎቹ ያዘወትሩታል። (የትግሬዎች ገዢ አባል ካድሬዎች ቀሳውስት፣ የእስልምና አመራር የገዥው አባላት - የኔ)

9. Corporate Power is Protected: የትልልቅ የንግድ ማኅበራት ባለቤቶች እንዳሻቸው መፈለል ይጠበቅላቸዋል

የፋሽስት መንግሥታት የኢንዱስትሪና የንግድ ስምሪቱ ባለቤት መኳንንት፤ አብዛኛውን ጊዜ መንግሥታዊ አለቆችን በቦታው ያስቀመጡ ናቸው፤ እናም በሁለቱ መካከል የጋራ የጥቅም እከከኝ ልከክህ ዝምድና ያበጃሉ። (ኤፈርት!!! ኤፈርት!!! ኤፈርት!!! - የኔ)

10. Labor Power is Suppressed: የሠራተኛው ተደራጅቶ ለመብቱ የመቆም ጉልበት እንዲሟሽሽ ይደረጋል

የሠራተኛው የማደራጀት ጉልበቱ ለፋሽስቱ መንግሥት ተጨባጭ አስጊ ስለሆነ፤ የሠራተኛ ማኅበራት ይወድማሉ ወይንም እጅና እግራቸው የተጠረፈ ይሆናል። (ራሱ ያደራጃቸው ካልሆኑ በስተቀር፤ ሌላ አለንዴ ለመሆኑ! የኔ)

11. Disdain for Intellectuals and the Arts: ለምሁራንና ለኪነ ጥበብ የሚያቅለሸልሽ ንቀትና ጥላቻ

የፋሽስት መንግሥታት ለከፍተኛ ትምህርትና ለዕውቀት ምጥቀት ግልጽ የሆነ ተቃዋሚነትን መገፋፋትና አለመቃወም። የፕሮፌሰሮች መታሰር፣ መባረር ሆነ መታፈን የተለመደ ነገር ነው። በኪነ ጥበብ ዙርያ ነፃ ሃሳብ ገለጻዎች በአደባባይ እንዲጠቁ ሲደረግ፤ መንግሥታት የኪነ ጥበባትን ሥራ ማካሄጃ ወጪ ይከለክላሉ፤ በእምቢታ ይነፍጋሉ። (በምን ተጀመረና! ዩኒቨርሲቲ መምህራንን በማባረር አይደለም እንዴ! - የኔ)

12. Obsession with Crime and Punishment: ለወንጀል ሥራና ለቅጣት ያላቸው አይታክት ትኩረት

በፋሽስት መንግሥታት ሥር፤ የፖሊስ ክፍል፤ ሕግን ለማስከበር ልጓም የለሽ ፈቃድ አላቸው። ሕዝቡም በሀገር መውደድ ስም የፖሊስን ከልክ ያለፈ ሰው ማጎሳቆል፤ ያልፉታል። የሕዝባዊ መብቶችንም መተውን ይቀበሉታል። በአብላጫው ጊዜ፤ ሊሹ የተለቀቀለት የፌዴራላዊ ፖሊስ አለ። (ትልልቆቹን አይበሉት እንጂ፤ እንደኔ ያለውንማ ማን ብሏቸው - የኔ)

13. Rampant Cronyism and Corruption: የተበሻቀጠ ሙስናና አድልዖ ማየል

የፋሽስት መንግሥታት ከሞላ ጎደል ሁልጊዜ፤ በጓደኞች ቡድንና ግብረ አበሮቻቸው የመንግሥት ሥልጣን የርስ በርስ ሹመት መቀባበል የሚገዙ ናቸው። መንግሥታዊ ሥልጣኑን እና ያላቸውን ኃላፊነት፤ ጓደኞቻቸውን ከተጠያቂነት ለመከለል ይጠቀሙበታል። በመንግሥት መሪዎች በኩል ያገሪቱ የተፈጥሮ ሀብቶች፤ የተካበቱ ንብረቶችም ጭምር መወሰዳቸው ወይም በቀጥታ መዘረፋቸው፤ በፋሽስት መንግሥታት ዘንድ ያልተለመደ አይደለም። *(ይሄን ሰው እንዳይሰማባቸው!!! ኢደባባዩ ኢያውቅባቸውም!!! - የኔ)*

14. Fraudulent Elections: የውሸት ምርጫዎች

*አንዳንድ ጊዜ፤ በፋሽስት መንግሥታት ውስጥ የሚደረጉ ምርጫዎች ሙሉ ለሙሉ የቀልድ ናቸው። በሌላ ጊዜ የተቃዋሚ ተወዳዳሪዎችን ስም ማጥፋትና አልፎ ተርፎም መግደሎችን በማከል፤ የድምጽ ሰጪዎችን ቁጥር መቀነስ፤ ሕጎችና መመሪያዎችን በማውጣት፤ የፖለቲካ አስተዳደር አካባቢዎችን ደንበር በማሸጋሸግና የሕዝብ ዜና መለዋወጫ ፈሰሶችን በመቆጣጠር መቀነስ ናቸው። (100%!!! ማቸነፍ!!! ከዚህ በላይ ቁጥር አለንዴ!!! - ወሊቃይት፣ ጠገዴ፣ ጠለምት፣ ራያ፣ መተከል የት ናችሁ? - የኔ)*

*ይህ ነው እንግዲህ ከሞላ ጎደል ከምሁራን ያገኘሁት የፋሽዝም ትርጉም። የትግሬዎች ገዥዎቻችንን ማለቴ ይሆን???*

ፋሽዝም በሂደት እየጠነከረ የሄደ፤ መንግሥታዊ ሥልጣኑ በአንድ የተባባሪዎች ቡድን የተያዘ ነው። የፋሽስቱ ገዥ አካል፤ ትክክለኛ የሕዝቡ ተወካይ የሆነውን የመንግሥት ክፍል ደምስሶ፤ ወይንም በጉልበት እወክለዋለሁ በማለት፤ በማንኛውም የሀገሪቱ የምጣኔ ሀብት ስምሪት ላይ አድራጊ ፈጣሪ ሆኖ ያዝበታል።[፳፮]

የፋሽዝምን ምንነትና ዕድገት፣ መሠረትና ጭብጥ ግንዛቤ ለማግኘት፤ ተመራማሪዎች በአንደኛውና በሁለተኛው የዓለም ጦርነቶች መካከል የነበረውን የአውሮፓ ኅብረተሰብ ሀቅ በመተንተን፤ የፋሽዝምን ክስተት ለመረዳት የሞከሩት፤ ሁለት የተለያዩ ድምዳሜዎች ላይ ደርሰዋል። የመጀመሪያው ወገን፤ "ቀኖና ወይንም ፍልስፍና ሳይሆን፤ ተግባር ነው አብዛኞዎቹን የፋሽስት ንቅናቄዎች የገፋፋቸውና የሚገልጻቸው!"[፳፯] የሚል ነው። ሁለተኛው ወገን ደግሞ፤ "የለም፤ የተግባር ሳይሆን፤ ርዕዩተ ዓለሙ ነው፤ በተለይም በግለሰቡና በኅብረተሰቡ መካከል ባለው ራዕይ ላይ፤ አንድ ንቅናቄ ራሱን ከሌሎች ለይቶ የሚያቆመው!"[፳፰] የሚል ነው። በተግባርና በርዕዩተ ዓለም መሠረት ፋሽዝምን ለመተንተን ምሁራን ልዩነት አብጅተዋል። ይህ የተመራማሪዎች ሚና ነው። በትክክል ለኛ ግንዛቤ የሚረዳን፤ መሠረታዊ ጉዳዩን በጥቅሉ በመረዳት፤ ግንዛቤያችንን ማስፋት ነው።

እኒሁ ተንታኞች፤ አሁን ያለውን የፋሽስት ዕድገት፤ በአውሮፓ አካባቢ ባሉ የናዚና የፋስስቶች ርዝራዦች ላይ ብቻ በማሽከርከር፤ ቀሪውን የዓለም ክፍል ዘለውታል። እኛ ከዚህ ምርምራቸው ተነስተን፤ ለኛ በሚመለከት መንገድ መቀየሱ የኛ ተግባር ነው። ወደ ተንታኞች ልመለስ።

የሁለቱን ወገን ለማመላከት፤ በመጀመሪያው በኩል፤ አንዳንድ ተንታኝ ምሁራን የጣሊያንን ፋሽዝም ሲተነትኑ፤ ከርዕዩተ ዓለም ይልቅ በተግባሩ ያተኩራሉ። ለነሱ፤ ለምሳሌ ለፓክስተን፤[፳፱] በጣሊያን የነበረውን የፋሽዝምን የዕድገት ሂደት በአምስት ደረጃ መርምረውታል።[፴]

ሀ) የእንቅስቃሴው መፈጠር
ለ) በፖለቲካ ስርዓቱ ሥር መስደዱ
ሐ) ሥልጣን መያዙ
መ) ሥልጣኑን በተግባር ላይ ማዋሉ
ረ) የረጅም ጊዜ ሕልውናው ( ግልብጥ ብሎ የመቀየሩ፤ ወይንም በዝግመት ሂደት የመለወጥ ዕድሉ )

እኒህን በየአንዳንዳቸው የደረጃ ትንተና ማድረጉ ለግልጽነቱ የሚረዳ ቢሆንም፤ ከላይ ቀደም አድርጌ ስለዘረዝርኩት፤ ተደጋጋሚና ተደጋጋፊ ትንታኔም ስለሆነ፤ ጠቅለል ባለ መልኩ አስቀምጠዋለሁ። ምንም እንኳ ለፋሺስት ንቅናቄ፤ ፅንሰ ሃሳብ አስፈላጊ ቢሆንም፤ ከረጋ የማስተዋል ምክንያታዊ ውይይቶች ይልቅ፤ ፋሽዝም በይበልጥ፤ "ፊት ለፊት በተከሰቱ ስሜታዊ ገጠመኞች"[፴፩] ይመረኮዛል። ይህ ብዙኀንን ለማነሳሳት ( ግለሰብን በዚህም በዚያም ምክንያት የቡድን ተገዢ  በማድረግ ) ቀና ይሆናል። ከስብስብ የርዕዩተ ዓለም አንድነት ይልቅ፤ የስብስብ የአንድነት ተግባር ነው ውህደት ሠጥቷቸው ንቅናቄውን ግለት የዳረገው ይላሉ፤ አባሪያቸው ሚካኤል ማን።[፴፪] በዚህ ዕድገት ሂደቱ፤ ተለዋዋጭ መልኮችን እየቀያየረ ሄዷል። እናም ፋሺዝም ከአንድ ወጥ መልክና ይዘት ይልቅ፤ የተጣመሩ ተለዋዋጭ ግንኙነቶች ይመስላል። በመጨረሻ በፋሽስቱ ጎራ የተገኙ

አብዛኛዎቹ ክፍሎች፤ የሚፈልጉት ምርጫ ቀርቦላቸው ሳይሆን፤ ከምርጫ፣ ምርጫ፣ በሂደት እየጠበበባቸው መጥቶ፤ ሌላ አማራጭ ከማጣት የተነተቱ ነበሩ፤ ሲሉ ያስቀምጡታል።

ለፓክስተን፤ ፋሽዝም እንደሌሎቹ ቅጥ የያዘ የፍልስፍና ሥርዓት "ኢዝሞች" ( ሶሺያሊዝም፣ ኮንሰርቫቲዝም፣ ሊበራሊዝም ) ዓይነት አይደለም። ፋሽዝም በአንድ የታሪክ ወቅት የተከሰተና የሚከሰት፤ በውጥረት ወቅት በሁለት ተፋጅ ክፍሎች፤ አክራሪ ነውጠኞችና በአጥባቂ ኋላ ቀሮች፤ መካከል የበቀለ የቀውጢ ሰዓት ድንጉር ሥርዓት ነው፤ በማለት ነው የሚያቀርቡት። አዲስ በተከሰተው የብዙኀን ፖለቲካ፤ ስሜታዊነት፤ በጥንቃቄ ተሰማምሮ የተቀነባበረ የስነ ሥርዓት ዝጉድጉድ፤ እና በጣም በጋለ ሁኔታ የሚደረግ ልፈፋ፤ በስሙ ተመርኩዘው ከቀረቡት ተጨባጩ እቅዶች እውነትነት ይልቅ የበለጠ ተደማጭነት አላቸው። ስለዚህ፤ ከርዕዩተ ዓላማ ስሌት ይልቅ፤ በተግባራቸው መተንተኑን መርጠዋል። ሰከን ባለ ውይይት ቦታ፤ ፋሽዝም ስሜታዊ አጣዳፊ ግኝትን በመተካት፤ ፖለቲካን የመታዘቢያ መድረክ ሚና ሠጥቶታል፤ ይላሉል።[፴፫]

ከላይ የጠቀስኳቸው ፓክስተን፤ ፋሽዝምን ከፍልስፍና ይልቅ ስሜታዊነት መሠረቱ ነው ብለው፤ በ፲፱፻፹/፹፩፤ "የፋሽዝም አምስት ደረጃዎች" ድርሰታቸው፤ ሰባት ስሜቶችን "የክተት መጥሪያ ቀስቃሾች" በማለት አስቀምጠዋቸዋል። እነሱም፤[፴፬]

፩. የቡድን የቅድሚያ የበላይነት፤ ከግል ወይንም ከሁሉን አቀፍ መብቶች ይልቅ ቡድኑን መደገፉ የበለጠ ጠቃሚ መሆኑ ስሜት ሲሠጥ፤

፪. የራስ ቡድን ተጠቅቷል ብሎ ማመን። ይህ ቡድኑ ጠላቴ ብሎ ባላቸው ላይ፤ ማንኛውንም እርምጃ መውሰዱን ትክክለኛ ነው ብሎ እንዲያምን ይረዳዋል፤

፫. ግለኝነት እና ሊበራሊም አደገኛ መላሸቅን ያመቻቻል ማለትና፤ በቡድኑ ላይ መጥፎ ተፅዕኖ ያስከትላል ብሎ ማመን

፬. ጠበቅ ያለ የማኅበርተኝነት ወይንም ወንድማማችነት ስሜት። ይህ ወንድማማችነት፣ "ውህደትና የነጠረ ጥራት፤ በጋራ ለመስዋዕት ዝግጁነት፤ ከተቻለ ወይንም ሌሎችን ባገለለ የእብሪት ጉልበት እንደብረት ጠንክረው ይወጣሉ።"

፭. የግለሰብ በራስ መተማመን፤ ከቡድን ግዙፍነት ጋር ተጣምሯል። ፓክስተን ይሄን "የዳለበ የማንነት እና የአባልነት ስሜት" ብለው እሳቸው ይጠሩታል።

፮. ሁልጊዜ፤ "በተፈጥሮው" ወንድ ያሉትን መሪ፤ ፍጹም ዓይንን ጨፍኖ መደገፍ። የዚህ ውጤት፤ አንድ ሰው ሀገር የማዳኑን ሚና እንዲወስድ ማድረጉ ነው።

፯. "ለሕልውና በሚደረግ ትግል፤ ለቡድኑ ስኬት ሲውል፤ ብጥብጥና ሆን ብሎ መግፋት ክብሩ" ያይላል፤ ብለው ፓክስተን ጽፈዋል። በተፈጥሮ በሌሎች ላይ የበላይነት ሃሳብ፤ በሂትለር ሁኔታ የተፈጥሮ ዘረኝነት፤ የፋሽስቶችን የዘገምታ ለውጥ ( ዳርዊኒዝም ) ግንዛቤ ይስማማቸዋል።

ሲሉ ዘርዝረዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ፤ የለም የሚሉና የፓክስተንን ከርዕዩተ ዓለም ይልቅ የተግባር ትንተና የሚቃወሙ፤ እንደ ስተርንሂል[፴፭] ያሉ አሉ። በነሱ ስሌት፤ የፓክስተን የተግባር ትንተና፤ በፋሽዝምና በአምባገነንነት መካከል ያለውን ልዩነት ለመግለጽ ብቁ አይሆንም። በርግጥ እንደ ስተርንሂል ላሉት፤ ማንኛውም ንቅናቄ መነሻ ርዕዩተ ዓለም አለው። ያን ይዞ ነው ሕዝቡን ማነሳሳት የሚችለው ባዮች ናቸው።

ፋሽዝም እንግዲህ፤ መንግሥታዊ ግዛቱን ከሁሉ በላይ አድርጎ ቆጥ ሰቅሎ፤ ግለሰቦችም ሆኑ የ"ሌላ" ሀገር ወይንም "ወገን" ሰዎች፤ ለዚሁ አካል ሙሉ በሙሉ አገልጋይና ሰጋጅ እንዲሆኑ የሚያደርግ አስተዳደር ነው። ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ፤ ጦርነትንና ሁከትን ሆን ብሎ በመፍጠርና በማራገብ፤ የመንግሥታዊ ግዛቱንና የወገኑን ልብ ለማነሳሳት ይጠቀምበታል። የዚህ ብሔርተኝነት ዝርዝሩ ግን ከሀገር ሀገር ይለያያል። በጥቅሉ ግን በግለሰቦች ላይና በ"ሌሎች" ላይ ጦርነት መክፈቱ አሌ የማይባልለት ባህሪው ነው።[፴፮]

ፋሽዝም የሚረዳው ነገር ቢኖር፤ "ግለሰቡ የሚሰግድለት ዓላማ ያስፈልገዋል። ስብስቡ ደግሞ በአንድ አምባገነን መንግሥት ሥር ተጠቃሎ፤ ያንን መንግሥታዊ ግዛት ጥሩ ተግባር ፈጻሚ ለማድረግ፤ ያ መንግሥታዊ ግዛት ደግሞ መፈራት፣ መከበር፣ እናም ሊሰገድለት ይገባል። ያ ነው ለሁሉ ሰዎች ጥሩ ሊሰራ የሚያስችለው!" የሚለውን ነው። ፋሽዝም የሚያመልከው ነገር ቢኖር፤ መንግሥታዊ ግዛቱ ከሁሉ በላይ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፤ በጣም ግዙፍ፣ የሚፈራና የበለጸገ እንዲሆን፤ ኃያል መሆን አለበት የሚለውን ነው። የመንግሥት ጥንካሬ ወሳኝ ነው ይላል። እንግዲህ በፍልስፍና ደረጃ፤ ከከበርቴውም ከላብ አደሩም

የወሰዳቸው አሉ። የራሱ የሆነ የለውም። የግራው ቅኝት ሰዎች፤ የከበርቴው አክራሪ ጽንፍ ነው ይሉታል። ( *እነሀ የግራ ሰዎች፤ ፋሽዝም፤ የሰዎችን መብት የማያከብር፤ አረመኔ፤ እና የበዝባዡን መደብ ያቀፈ፤ የሠራተኛው መደብ ጠላት ብለው ያስቀምጡታል።* ) በቀኝ ያሉት ደግሞ፤ ከግራው ርዕዩት የጎረሰ ነው ይሉታል። ( *እነሀ የቀኝ ሰዎች፤ ፋሽዝምን፤ የሶሺያሊዝም አንድ ገጽ ነው፤ ብለው ይመድቡታል። በነሀ ሰዎች አመለካከት፤ ሶሺያሊዝም የሰዎችን ንብረት በቀጥታ በመንግሥት ስም ሲወርስ፤ ፋሽዝም ደግሞ፤ ለሀገሪቱ ሲባል ሰዎች መስዋዕት እንዲያደርጉ በማለት፤ የሀገሪቱን ንብረት ለይስሙላ በባለቤትነት በተቀመጡ የራሱ ኃብታሞች እንዲይዙት ይወርሳል፤ ይላሉ። ሶሺያሊዝም የገቢያ ግንኙነትን ፈጽሞ ሲያጠፋ፤ ፋሽዝም ግን ለይስሙላ ያለ የሚያስመስል የዚያው ግርፍ ነው፤ ይላሉ።* ) እንደምረዳው ሁለቱም አይወዱትም። ሁለቱም የኔ ወገን አይደለም ይላሉ። ለኛ በቂ ማስረጃ አግኝተናል።

በርግጥ የፖለቲካ ድርጅት መሪዎችና የታሪክ ልሂቃን፤ ስለ ፋሽዝም በዝርዝር አጥንተው አቋም ለመውሰድና የትግል አቅጣጫን ለመቀየስ፤ ወይንም ትምህርት ለመሥጠትና ትክክለኛውን ለመረዳት ይጠቀሙበታል። ለኛ ትምህርቱ፤ ተመሳሳይ ክኖች፤ ተመሳሳይ ውጤትን ያስከትላሉ የሚለው ነው። ትምህርታችንም ከዚህ ይመነጫል። በይስሙላ ትግል ሰመመን እያንቀላፋን እና ይይስሙላ የትግል ጉዞ እያደረግን፤ ወደፊት መሄድ አንችልም። ከዚህ ተነስተን የትግሬዎችን ገዥዎች ስንመረምር፤ በማያወላዳ ሁኔታ ፋሽስት ሆነው እናገኛቸዋለን።

ለምንና እንዴት ተብሎ?

የትግሬዎቹ ገዥዎች አዲስ አበባ በገቡ ጊዜ፤ ከፍተኛ የሆነ አለመረጋጋት በሀገሪቱ ነበር። ሥራ አጦቹ የትዬ ለሌ ነበሩ። ስነ ሥርዓት አልነበረም። ሕዝቡ "ምን ይከተል ይሆን!" በሚል ፍርሃት ተውጦ ነበር። ደርግ ከቆሰቆሳቸውና ከተቆሰቆሱበት ጦርነቶች ጋር በተያያዘ፤ ብዙ ወታደራዊ ልምድ ያላቸው የታጠቁና ያልታጠቁ ሥልጡን ሰዎች፤ በከተማና በገጠር በየጎዳናው ነበሩ። በርግጥ ኢትዮጵያን በዚያን ወቅት የወረረ ጠላት አልነበረም። በቅብጥብጡ የሶማሊያ መንግሥት የተደረገው ወረራ፤ ተነኳኩቶ የራሱን መንግሥት አውድሞ፤ ሀገሯን ራሷን ሶማሊያን የፈረሰ ባድማ አድርጓታል። አደጋ ራሱ ባየሩ ላይ እያንጃበበ፤ ሕዝቡን አስጨንቆት ነበር። ሀገር እና ኢትዮጵያ የሚለው ድንግርግር ያለበት ሰዓት ነበር። ሕዝቡ ግራ የተጋባበትና በመንግሥት ላይ እምነት ማጣት ያየለበት ወቅት ነበር። ይህ ሁኔታ ከሁሉም ድርጅቶች አረመኔ ለሆነው ጉልበተኛ አመቺ ነበር። ለእድገቱም ለምለም መሬት ነበር። ፋሽስቶች ሜዳውን ክፍት ሆኖ አገኙት። እናም ፏለሉበት።

ይሄን ሁሉ ካልኩ በኋላ፤ በዚህ ጽሑፍ የትግሬዎችን ገዥ ቡድን ስመለከት፤ ከሶስት ማዕዘኖች ተነስቼ ነው። ከፍልስፍናው፣ ከተግባሩና ከፍላጎቱ። በዚህ ሂደት፤ ይህ የትግሬዎች መንግሥት፤ ***ፋሺስት*** መሆኑን አሳያለሁ።

፩ኛ. ከአነሳሱ፤ የትግሬዎቹ ቡድን፤ በመደቦች መካከል የነበረውን ትግል ቀየረውና አደበዘዘው። ቅድመ የካቲት ፲፱፻፷፮ ዓመተ ምህረት፤ በገዥው ክፍልና በቀሪው ኢትዮጵያዊያን መካከል፤ አልገዛም በቃኝ አይሎ፤ ሕዝቡ ባንድነት፤ የመብት ነፃነቱን አዝሎ፤ የራሴ ሕዝባዊ መንግሥት መመሥረት አለብኝ ብሎ የተነሳበት ሀቅ ነበር። በዚያ ወቅት በመሬት ምርት ላይ የተመሠረተው የሀገራችን ምጣኔ ሀብት፤ መሬቱን በሚያርሱ ገበሬዎች ላይ ነበር ተደላድሎ የቆመው። ይህ ደግሞ፤ በጢሰኛው እና በቦታው በሌለው የመሬቱ ባለቤት መካከል ባፈጠጠ "ያሻኝን አደርጋለሁ!" "ምን አባህ!" ጉልበት ላይ የተተከለ ግንኙነት ሲሆን፤ በተደራቢ ደግሞ፤ የሠራተኛው ያለ ስምምነት አሠሪዎቹ እንዳፈተታቸው የሚያደርጉት ግፍ ተከታዩ ነበር። እንግዲህ በተወሰነ ደረጃ ደግሞ፤ አብዛኛውን የሀገሪቱን ሠራተኛ ክፍል የቀጠረው የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት፤ በመምህራን፣ በሕክምና ባለሙያዎች፣ በማዘጋጃ ቤት ሠራተኞች፣ በጋዜጠኞች፣ በጦር ኃይልና ፖሊስ አባላት ዘንድ፤ የኔ አገልጋዮች ብቻ ሁኑ! የሚል ግንኙነት ነበራቸው።

ይህ ሁሉ አንድ ደረጃ ላይ ደርሶ፤ ሕዝቡ፤ "ገዢዎቻችን ሌቦች ናቸው። ሰርቀው ሰርቀው አይበቃቸው!" በማለት፤ ወጊዱ አላቸው። ይህ ሕዝባዊ እምቢተኝነት፤ ትክክለኛና ሀገሪቱን ወደፊት የሚወስድ ነበር። ደርጋማው መንግሥቱ ኃይለማርያም፤ "እኔ ነኝ ኢትዮጵያ! እኔ ብቻ ነኝ አዋቂ!" አለና፤ ሀገሪቱን በታትኖ ለትግሬዎቹ ቡድን ቦታውን ለቀቀላቸው። ደርጋማው መንግሥት፤ ከአረመኔያዊ ተግባሩ ጎን፤ ብዙ መሠረታዊ የነበሩ የኅብረተሰቡ እውነታዎችን ቀይሯል። በተለይም የመሬት አዋጁ፤ ምንም እንኳን በደንብ ያልተጠናና በትክክል በሥራ ላይ ያልዋለ ( ከጅምሩም እቅዱ ይሄ አልነበረምና ) ቢሆንም፤ በመሬቱ ላይ የተመሰረተውን የባላባትና የጢሰኛ ግንኙነት፤ ላንዴና ለሁሌም ደምስሶታል። የሃይማኖት ተቋሙንም ሚና ከመንግሥት አስወጥቶታል። በዚያው ልክ፤ የአሁኑን የትግሬዎቹን መንግሥት እንደተነተንኩት ሊተነተን የሚችል መንግሥታዊ ግዛት መሥርቶ፤ በሕዝቡ መካከል የነበሩ የኅብረተሰቡ ዕሴቶችን አጥፍቷል። በዚህ ወቅት ነው እንግዲህ የትግሬዎቹ መንግሥት የተመሠረተው።

እንግዲህ ይህን የመደብ ትግል፤ የትግሬዎቹ ቡድን ቀየረው። አደበዘዘው። ትግሬ ከሆንክ፤ ሀብታም ሁን ደሃ፤ አንድ ነህ። ተጨቋኝ ነህ። ኦሮሞ ከሆንክ እንዲሁ። አማራ ከሆንክ፤ መገዘዝ ተራራ ላይ ሰውነትክን እንደዕቃ አስረህ በትንሽ መቆፈሪያ እህል ብታመርትም፣ ደብረመይ ጎብጠህ በፈረስ ብታርስም፣ በየዳ ከብርድ ጋር እየታገልሽ በበጎችሽ በጠጥ እንጀራሽን ብትጋግሪም፣ ቆማ ፋሲለደስ ከሁሉም ነገር ርቀህ የመኪና መንገድ እንኳን ሳታይ አምላክህን ብትለምንም፣ የአላማጣን ተራራ ደፋ ቀና ብትልበትም፤ "አንተ አማራ ጨቋኝ ነህ!" የሚል ተለጠፈበት። ይህ ከሶሺያሊስቶችም ሆነ ከከበርቴዎች ፍልስፍና አንጻር የቆመው የፋሽዝም ፍልስፍና አንዱ መለያው ነው።

፪ኛ. በፋሽስት ሥርዓት፤ ያመቸ መንገድ ሁሉ ይወሰዳል። በመንግሥት ላይ ጭፍን እምነትና አምልኮ እንዲኖር ያደርጋሉ። "እኛ ከሌለን . . . !" ብለው የለ! ድጋፍ ለማስገኘት የዘየደበት አንዱ መንገድ፤ በደርግ ጊዜ የተደመሰሰውን የነፍጠኛና የጢሰኛ ግንኙነት፤ ልክ እንዳለ አድርጎ፤ ***ነፍጠኛ ኢድጋሪዎች*** መጡባችሁ! ጠላቶቻችሁ እነሱ ናቸው! ብሎ መቀስቀስ ብቻ አይደለም፤ ዛሬም ድረስ ይሰብክበታል። ደርግም ወድሞ፤ አዲስ ሕልውና ተሠጥቶት፤ አማራ በሚል ትርጉም ታጅሎ፤ ጠላት ሆኗል። ቤተክርስትያናት ተቃጥለዋል። መስጊዶች ተቃጥለዋል። ሕፃናት ታርደዋል። አዛውንት ገደል ተጥለዋል። የሰው ሥጋ ታርዶ ተበልቷል። አሁንም ደመሰስናቸው ያሏቸው ደርግና አማራ፤ ዘለዓለማዊ ሕልውና ተሠጥቷቸው፤ ማስፈራሪያና ሕዝብን ማነሳሻ ሆነዋል። ጉልበትንና ሁከትን መጠቀም፤ የፋሽስቶች ዓይነተኛ መንገድ ነው። እዚህ ላይ ስብሃት ነጋ፤ "የአማራን እና የኦርቶዶክስ ቤተክርስትያንን አከርካሪ መተነዋል!" ማለታቸውን መጥቀስ ይጠቅማል። ይህ የፋሺስቶች ባህሪ ነው።

፫ኛ. ሕዝቡን ለመያዝ፤ ገና ደደቢት እያለ፤ ካድሬዎቹን አሠልጥኖ፤ ሃይማኖታዊ ተቋማትን መቆጣጠር ያዘ። ለእምነት ተቆርቋሪነት ኖሮት ሳይሆን፤ ሕዝቡን ለመያዝ ዓይነተኛ መሳሪያ ስለሆነ ነበር። እናም መጀመሪያ የትግራይ ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያንን ለማቋቋም፤ በኋላ ላይ በለስ ቀንቶት አዲስ አበባ ሲገባ ደግሞ፤ የነበሩትን የቤተክርስትያኗ ካህናት፤ ከፓትሪያርኩ እስከ የቤተክርስትያኗ ቅጥር ግቢ ጠባቂ አባሮ፤ በትግሬዎቹ አባሎቹ ሞላው። በኋላ ላይ እንዳየነውም፤ የእስልምና ተከታዮችን ተቋምም፤ በቀጥታ ዘው ብሎ ገብቶ፤ ቀኖናቸውንና የአመራር አባሎቻቸውን ለውጦ፤ እንደ ክርስትያኖቹ ተቋም ሁሉ፤ በራሱ ምስል ጠፍጥፎ ተቀበሉኝ አለ። ይህ ዓይነተኛ የፋሺስት እምነትና ባህሪ ነው።

፬ኛ. ሕዝቡን እንደ የጦር ሠራዊቱ አባሎች አንድ ለአምስት ጠርንፎ ማዋቀርና መቆጣጠር። ግለሰብ፤ የትም ሆነ የትም፤ ነፃነት የለውም። መንግሥታዊ ግዛቱ የፈለገውን ያደርጋል። ይህ ሕዝቡ በሙሉ ቀጥ ብሎ እንደ አንድ ግለሰብ በመንግሥት ትዕዛዝ እንዲንቀሳቀስና፤ መንግሥት የሕዝብ የበላይ እንጂ፤ ሕዝብ የመንግሥት የበላይ እንዳልሆነ የሚያረጋግጠው የፋሽስት ሥርዓት እምነት ነው። ሕዝቡን ከላይ ወደታች ቀጥ ያለ መዋቅር አበጅቶ፤ እንደ ጣዖት የሚመለክ ገዥ አስቀምጧል።

፭ኛ. ሙሉ በሙሉ በግለሰብ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች፤ እምነት አለመኖር። በትግሬዎቹ ገዥዎች እምነት፤ የግለሰብ መብት ቅንጦት ነው። በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ወይንም በነሱ ማዕከላዊነት ሂሳብ፤ ልማትና ስለ ሥርዓት እንጂ፤ መብት ቦታ የለውም። ይህ ቁልጭ ያለ የፋሽዝም መለያ ነው።

፮ኛ. በተጠቂነት ራስን መመልከትና፤ የአስተዳደር ዘይቤን በዚያ ማነጽ። ትግራይ ቀድሞ ገዥ ነበረች። ቀድሞ እኛ ብቻ እንጂ ሌሎች አልነበሩም። ማዕከሉ ብቻ ሳይሆን ሁሉም ነገር የኛ ነበር። አሁን አማራ ሥልጣን ነጠቀን። ሚኒሊክ የትግሬዎችን ሥልጣን ወደ ሸዋ አዛወረው የሚል "ተበደልን" ቁጭት! የሞሶሎኒ አንዱ ቁጭት፤ ጣሊያን በአንደኛው የዓለም ጦርነት ካቸናፊዎቹ ጋር ተዋግተን፤ ሌሎቹ ሲጠቀሙ፤ እኛ ግን ባዶ መቅረታችን ብቻ ሳይሆን፤ ለጦርነቱ ስንል ባወጣነው ተጎዳን፤ የሚለው ነበር። ፋሽዝም በገጠጠ መልኩ! አሁን ደግሞ ትግራይ ተጎድታለችና፤ ልዩ ጥቅም ያስፈልጋታል በሚል ተተክቷል።

፯ኛ. "ተጋዳላይ" መሆን መጠቀሚያና ትልቅ ክብር መሆኑ። "እንደኛ በርሃ ግቡ!" "እኛ ስንቶቹን ገብረን ያገኘነውን ሥልጣን!" "መንገዱን ጨርቅ ያድርግላችሁ!" "የትግሬዎቹ ጦር ከሁሉም የላቀ ጀግና!" እነዚህ ሁሉ ጦርነትን እንደ ጀብዱ፤ ተዋጊዎቹን እንደ ተዓምር ሠሪዎች ማንቆለጳጰሱ የፋሽስቶች ባህሪ ነው። ዛሬ በኢትዮጵያ፤ ጄኔራሎቹ የትልልቅ ሕንጻዎች እና የሰፋፊ የርሻ መሬቶች ባለቤቶች ናቸው።

፰ኛ. ከላይ፤ የፋሽስቶች ብሔርተኛነት "በኔ እምነት ለትንተና ሙቀት እንደተሠጣ ነው።" ያልኩትን ተመርኩዤ፤ ይህ የትግሬዎች ገዥ ቡድን፤ ሀገራዊ ብሔርተኝነት አልነበረውም። የለውም። ሊኖረው እንደማይችል ግልጽ ነው።

ትግሬ እንጂ ኢትዮጵያዊ አይደለምና! እናም ትግሬ መሆኑን አስመልክቶ፤ "እንኳን ከናንተ ተወለድኩ። እንኳን ከናንተ ከወርቆቹ ተፈጠርኩ!" የምትለው አባባል፤ በበቂ ሁሉን ታስረዳለች። ጠባብ ብሔርተኝነት አላቸው። ያከረረ ትግሬነትና የትግሬዎችን የበላይነት ይገፋሉ። በዚች ጢስ የነሂትለርን የዘር ጥራት ማስታወስ ይቻላል። ይህ የፋሽስት እምነት ነው።

፱ኛ. የሀገሪቱን ምጣኔ ሀብት መቆጣጠር። ለዚህ ሁሉም የሚያለቅስበት ስለሆነ፤ "ኤፈርት!" ብቻ ብሎ ማለፉ በቂ ነው።

፲ኛ. የዜና ማሰራጫዎችን በሙሉ በቁጥጥሩ ሥር አድርጎ ለራሱ ሰብከት ብቻ ማዋሉ። የነፃ ጋዜጦች ከነጋዜጠኞቻቸው ድራሻቸውን አጠፋ። ሬዲዮው የሚዘምረው የትግሬዎቹን ትልቅነት ነው። የሚደረሱት መጽሐፍት በሙሉ ለትግሬዎች ሰብከት ነው። በነገራችን ላይ፤ ትግራይ ተከዜን ተሻግሮ፤ የራስ ደጀንን የትግራይ ክልል መሆን ተማሪዎች እንደተማሩ፣ መምህራን እንዳስተማሩ፤ ከንጉሠ ነገሥት ዮሐንስ በቀር ሌሎች የኢትዮጵያ ነገሥታት በሙሉ መጥፎ እንደሆኑ መጽሐፎች መደረሳቸውን የማያውቅ ይኖር ይሆን! ተራራው ተከዜን ተሻግሮ ከሄደ፤ ምን የማይቻል ነገር አለ! ፋሽዝም በገሃዱ!

፲፩ኛ. ማንኛውንም የሰዎች ስብስብ ከመንግሥት ቁጥጥር ውጪ አለመፍቀድ። የነፃ ጋዜጠኞች ማኅበር፣ የመምህራን ማኅበር፣ የሠራተኞች ማኅበር፣ የተማሪዎች ማኅበር፣ የሴቶች ማኅበር፣ አለመኖሩን ማተት ለቀባሪው መንገር ይሆንብኛል። ፋሽዝም በማያወላውል መልኩ!

ከነዚህ ማስረጃዎች በተጨማሪ ሌሎች አነስ ያለ ክብደት ያላቸውን መዘርዘር ይቻላል። ለምሳሌ አላስፈላጊ የሆነውንና በጌቶቹ ትዕዛዝ ያደረገውን የሱማሌ ወረራ አስመልክቶ፣ ከመቶ ሺ በላይ ወጣቶች የታረዱበትን የባድሜ ጦርነት አስመልክቶ፣ ከጫፍ እስከጫፍ የኢትዮጵያን ንብረት ሰርቆ ወደ መቀሌ ማጓጓዙን አስመልክቶ፣ . . . ወዘተ.። ነገር ግን መደረት ስለሚሆን አልፈዋለሁ። ምናልባት ይህማ የአምባገነን ተግባር አይደል! የምትሉ ልትኖሩ ትችላላችሁ። ደግ ነው። ፋሽስት እኮ ከአምባገነንም አምባገነን ነው። ሆኖም ግን፤ በፍልስፍናው፣ በተግባሩና በእምነቱ ከከበርቴውና ከሶሺያሊስቱ የተለዩ ሲሆን፤ አምባገነኖች ከሞላ ጎደል የከበርቴው ሥርዓት አክራሪ አጽናፍ ናቸው።

**ማጠቃለያ፤**

በኢትዮጵያ የዘር ፖለቲካ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲከሰት፤ ሕዝቡም ሆነ የፖለቲካ ድርጅቶች ለግንዛቤው ተጎታች ነበርን። በርግጥ ጠንጣኙ የትግሬዎች ገገር ቡድን ዝግጁ ነበር። ለሀገሪቱ እንግዳ ይሁን እንጂ፤ ይህ የትግሬዎች ገዥ ቡድን፤ ገና ከጠዋቱ ሲፈጠር የጎነጎነው ሴራ ነበር። የሀገሪቱ የፖለቲካ መድረክ ባዶ ነበር። ይሄንን ተጠቅሞ የትግሬዎቹ ገዥ ቡድን፤ የራሱ የሆነ የአገዛዝ ስልት አስቀመጠ። ከላይ በተዘረዘሩት መስፈርቶች ስመዝነው፤ ይህ የትግሬዎች ቡድን የያዘው የፋሽስት መንግሥታዊ ግዛት ነው። ነጥቦቹ በሙሉ ተመትተዋል። ጭካኔውና ፍጅቱ ብቻ አይደለም። የሀገሪቱን የተፈጥሮ ሀብት መቆጣጠሩ ብቻ አይደለም። ትግሬ ባልሆኑት የሀገሪቱ ዜጎች ላይ ያደረሰው በደል ብቻ አይደለም። የወንድን ፍጹም የበላይነት ማስፈኑና፤ ዝሙትነትን ማስፋፋቱ ብቻ አይደለም። ሰውን ማሳደዱ ብቻ አይደለም። ግድያውና እስራቱ ብቻ እይደለም። ትግሬዎቹን ለይቶ ተጠቃሚዎች ማድረጉ ብቻ አይደለም። ምንም ዓይነት ተቃዋሚ እንዳይኖር ማድረጉ ብቻ አይደለም። የተለየ የኢጋዚ ጦር ማዘጋጀቱና በሕዝቡ ላይ ይሄ ነው ተብሎ የማይገመት ስቃይ ማድረሱ ብቻ አይደለም። ዐማራውን ለይቶ ማጥቃቱ ብቻ አይደለም። አኙዋኩን ለይቶ ማጥቃቱ ብቻ አይደለም። ኦሮሞውን ለይቶ ማጥቃት ብቻ አይደለም። የቀረው ምን አለ!

ይህ ሥርዓት፤ ሀገራችን ከፍተኛ እንጥልጥል ላይ በነበረችበት ሁኔታ፣ ሕዝቡ ለነፃነቱ ከምን ጊዜም በላይ ነቅቶ በተነሳበት ሰዓት፣ የሀገሪቱ አስተዳደር በተምታታበት ወቅት፣ ገዢው ክፍል ቦታውን ለቆ፤ ባዶ አድርጎ በሄደበት ጊዜ የተከሰተና፤ በ፲፩ ቱ ነጥቦች ሚዛን ሲለካ፤ አሟልቶ የሚገኝ የቀውጢ ሰዓት ሥርዓት ነው። ተቀናቃኞቹን ምን እንዳደረጋቸው ሁላችን እናውቃለን። ቲ.ኤል.ኤፍ.፣ ኢ.ዲ.ዩ.፣ ኢ.ሕ.አ.ፓ.፣ ኢ.ኤል.ኤፍ.፣ ቅንጅት፣ መድረክ፣ አረና፣ ዝርዝሩ አያልቅም። የሀገራችንን ሀብት ምን እንዳደረገ ሁላችን እናውቃለን። ኤፈርት!!! መሪዎቹ የሀገሪቱ ዋና ዋና ሀብታሞች እንደሆኑ እናውቃለን። ሕዝቡ አማራጭ አጥቶ ወደ አክራሪ ሃይማኖተኛነት እየተገደደ መሄዱን እናውቃለን። መብት የሚባል ከነጭራሹ የጠፋ መሆኑን እናውቃለን። ፍርሃት በኢትዮጵያ እንደነገሠ እናውቃለን። ሰው ለራሱ ለግሉ ለመኖር እንጂ፤ ለሚኖርበት ኅብረተሰብ ሕልውና ደንታ የሌለው እንዲሆን እየተደረገ መሄዱን እናውቃለን። ወጣቱ በጫት፣ በዝሙት፣ በራስ ወዳድነት እንዲለከፍ መደረጉን እናውቃለን። እናም ለኔ ይህ፤ በፖለቲካ ፍልስፍናና በአስተዳደር መመሪያ የተቀነባበረ የፋሽስት ሥርዓት ውጤት ነው።

## ማመላከቻዎች

ፋሽዝም በቂ ጥናት የተደረገበት ስለሆነ፤ ብዙዎቹ ሃሳቦች በተለያዩ መጽሐፍት፤ ድረገጾችና መጽሔቶች ተደጋግመው ሰፍረዋል። የተለያዩ ጸሐፍት ውለውበታል። እናም በብዙ ቦታ አንድ ሃሳብ ሰፍሮ ይገኛል። ለዚህ ጽሑፈ የሚከተሉትን ማስደገፊያዎች አገላብጫለሁ። በቁጥራቸው መሠረትም ማብራሪያ አክያለሁ።


፩. http://www.worldfuturefund.org/wffmaster/Reading/Germany/mussolini.htm

፪. የላይኛው

፫. አጉስቶ ፒኖቼ፤ አጉስቶ ሆሴ ራሞን ፒኖቼ ኡጋርቴ፤ ( ሕዳር ፲፱፻፰ እስከ ታህሣስ ፲፱፻፺፱ ) የቺሊ ጀኔራል፤ ከ፲፱፻፷፮ እስከ ፲፱፻፹፫ ድረስ ቺሊን በአምባገነንነት፤ የጦር ኃይሎች ዋና አዛዥ፣ ፕሬዘዳንት፣ በመሆን የገዙ ፋሽስት መሪ ነበሩ።

፬. ፍራንሲስኮ ፍራንኮ፤ ፍራንሲስኮ ፍራንኮ ባሃሞንዴ፤ ( ታህሣስ ፲፰፻፹፭ እስከ ሕዳር ፲፱፻፷፰ ) ከ፲፱፻፳፱ እስከ ዕለተ ሞታቸው ( ፲፱፻፷፰ ) ድረስ ለ፴፱ ዓመታት በአምባገነንነት የገዙ ፋሺስት ነበሩ።

፭. ጂን ቦዴል ቦካሳ፤ ጂን ቦዴል ቦካሳ፤ ( የካቲት ፲፪ ቀን ፲፱፻፲፫ እስከ ጥቅምት ፳፫ ቀን ፲፱፻፹፱ ) በመፈንቅለ መንግሥት ጀምሮ፤ ዓለም አላውቅልዎትም ያላቸውን ንጉሠ ነገሥትነት ያወጁ፤ የማዕከላዊ አፍሪካ ሩፑብሊክ፤ በአምባገነንነት የገዙ ፋሺስት መሪ ነበሩ።

፮. አሳድ አባትና ልጁ፤ አባትየው ሃፌዝ አል አሳድ እና ልጅየው በሺር አል አሳድ፤ ሶሪያን አባት ለልጁ በማስተላለፍ፤ ከ፲፱፻፷፫ ጀምረው እስከዛሬ ድረስ፤ በአምባገነንነት ፋሺስታዊ የመንግሥት ሥርዓት ያካሄዱና እያካሄዱ ያሉ ናቸው።

፯. የኪም ቤተሰብ፤ የኪም ቤተሰብ ደግሞ ሶስት ትውልድ ያቀፈ ነው። አያታቸው ኪም ኢል ሶንግ፣ አባታቸው ኪም ጆንግ ኢል ( ከሳቸው ጀምሮ ቀጣይ ገዢዎች በሙሉ፤ የኮሪያ ዴሞክራሲያዊ ሕዝባዊ ሩፑብሊክ፤ ፍጹም የበላይ መሪ በመባል እንዲጠሩ ደንግገዋል)፣ እሳቸው ደግሞ ኪም ጆንግ ኧን፣ ሶስቱ ኮሪያን ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ( ፲፱፻፴፯ ) ጀምሮ እስካሁን ድረስ፤ እንደ ብረት ቀጥቅጠው የገዙና እየገዙ ያሉ ፋሽስቶች ናቸው።

፰. ሱሃርቶ፤ ሃጅ ሙሐመድ ሱሃርቶ፤ ( ግንቦት ፳፯ ቀን፤ ፲፱፻፲፫ እስከ ጥር ፲፯ ቀን ፳፻ ) ለ፴፩ ዓመታት ኢንዶኔዥያን ( ፲፱፻፷ እስከ ፲፱፻፺፩ ) ቀጥቅጠው የገዙ ፋሺስት ነበሩ።

፱. ፖል ፖት፤ ፖል ፖት፤ ( ግንቦት ፲ ቀን ፲፱፻፲፯ እስከ ሚያዝያ ፯ ቀን ፲፱፻፺ ) በትውልድ ስማቸው ሳሎትዝ ሳር የሚባሉ፤ ከ፲፱፻፷፯ እስከ ፲፱፻፸ ድረስ ክሐመር ሩጅን ( ካምቦዲያን ) ቀጥቅጠው የገዙ የግራው ፋሽስት ነበሩ። የከተማውን ሰው በሙሉ ጠራርገው ወደ ገጠር በመስደድ፤ ብዙ ሰው የፈጁ ነበሩ።

፲. ጆሴፍ ስታሊን፤ ጂሴፍ ቪሳሪዮኖቪች ስታሊን፤ ( ሕዳር ፰ ቀን ፲፰፻፸፩ እስከ መጋቢት ፲፱፻፵፭ ) ድረስ የሶቪየት ሩፑብሊክን - ከ፲፱፻፲ሮቹ መጨረሻ እስኪሞቱ፤ የካቲት ፳፭ ቀን አካባቢ ፲፱፻፸፭ ድረስ ቀጥቅጠው የገዙ፤ በስም ኮምኒስት፤ በተግባር አረመኔ ፋሺስት ገዥ ነበሩ።

፲፩. Paxton, Robert O. The Anatomy of Fascism, irst Vintage Books, March 2005, www.vintagebooks.com

፲፪. http://www.diffen.com/difference/Communism_vs_Fascism

፲፫. https://www.marxists.org/archive/trotsky/works/1944/1944-fas.htm

፲፬. የላይኛው

፲፭. የላይኛው

፲፮. የላይኛው

፲፯. የላይኛው

፲፰. የላይኛው

፲፱. http://www.worldfuturefund.org/wffmaster/Reading/Germany/mussolini.htm

፳. http://www.urbandictionary.com/define.php?term=Adolph+Hitler

http://study.com/academy/lesson/german-fascism-under-hitler.html

፳፩. From Encyclopedia Italia 1932:

፳፪. https://www.marxists.org/glossary/terms/f/a.htm

፳፫. http://www.livescience.com/57622-fascism.html

፳፬. http://www.anesi.com/Fascism-TheUltimateDefinition.htm

፳፭. http://www.rense.com/general37/char.htm

፳፮. https://www.marxists.org/glossary/terms/f/a.htm

፳፯. http://www.livescience.com/57622-fascism.html

፳፰. የላይኛው

፳፱. Paxton, Robert O. The Anatomy of Fascism, irst Vintage Books, March 2005,

www.vintagebooks.com

፴. የላይኛው

፴፩. http://www.spectator.co.uk/2004/05/the-five-stages-of-a-downhill-descent/

፴፪. Mann. Michael, Fascists, CAMBRIDGE UNIVERSITY PRESS 2004, 32 Avenue of the Americas, New York, NY 10013-2473, USA

ሙሉ መጽሐፉን ለማንበብ፤ http://socioline.ru/files/5/283/mann_michael_-_fascists_-_2004.pdf

፴፫. Sternhell, Zeev; Neither Right nor Left: Fascist Ideology in France, Translated by David Maisel. With a new preface by the author, Princeton books, Hardcover published in 1986 by California

፴፬. http://www.livescience.com/57622-fascism.html

Paxton, author of several books, including "The Anatomy of Fascism" (Vintage, 2005), said fascism is based more on feelings than philosophical ideas. In his 1988 essay "The Five Stages of Fascism," published in 1998 in the Journal of Modern History, he defined seven feelings that act as "mobilizing passions" for fascist regimes.

፴፭. Sternhell, Zeev; Neither Right nor Left: Fascist Ideology in France, Translated by David Maisel. With a new preface by the author, Princeton books, Hardcover published in 1986 by California

፴፮. http://www.livescience.com/57622-fascism.html


*ተጨማሪ ጠቃሚ ማስረጃዎች፤*


Knox, MacGregor. Common Destiny: Dictatorship, Foreign Policy, and War in Fascist Italy and Nazi Germany. Cambridge, UK: Cambridge UP, 2000. 125. Print.

http://www.ocs.cnyric.org/webpages/phyland/files/the%20rise%20of%20fascism1.pdf